# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሴቶች ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

## በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆኑና ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ ለማድረግ ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 133/2015 ዓ.ም

ጥቅምት 2015 ዓ/ም

አዲስ አበባ

የከተማችንን ልማት ለማፋጠንና የመልካም አስተዳደር ስርዓት ግንባታችንን ለማጎልበት የሴቶችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ የሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎችና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡

በከተማችንም ለሚከናወኑ የልማት ፣ የመልካም አስተዳደርና የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታዎች የህብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑትን ሴቶች በሁሉም ዘርፎች በቀጥታ በማሳተፍ ሴቶች የልማቱ ተሳታፊና ተጠቃሚ ሲሆኑ የሚችሉበትን አሰራርና አደረጃጀት በመፍጠር የሴቶችን ተሳትፎ ላቅ ወደ አለ ደረጃ ማሳደግ የሚያስፈልግ በመሆኑ፤

ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ችግራቸውን አጣርቶ የኢኮኖሚ አቅም የሚፈጥሩበትን የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ የተሻለ ህይወት እንዲመሩ ለማድረግ በአፈጻጸምና አስተዳደር ሂደት ላይ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለመፍታት እንዲሁም ክትትልና ድጋፍ ለመስጠት አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የአዲስአበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአስፈጻሚአካላት ለማቋቋም እና ስልጣንና ተግባራቸውን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ (2) ፊደል ተራ (ሠ) በተሰጠዉ ስልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## <u>ክፍል አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ</u>

### 1. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ለሆኑና ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች የገንዘብ /የቁሳቁስ/ ድጋፍ ለማድረግ ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 133/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ፡፡

### 2. ት<u>ርጓሜ</u>

በዚህ መመሪያ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጥ ካልሆነ በስተቀር፡-

1. "ከተማ" ማለትየአዲስ አበባ ከተማ ነው፡፡
2. "ክፍለ ከተማ" ማለት የከተማው ሁለተኛ ደረጃ አስተዳደር እርከን ነው
3. "ወረዳ" ማለት የከተማው ሶስተኛ ደረጃ የአስተዳደር እርከን ነው፤
4. "ቢሮ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ነው፤
5. "ጽህፈት ቤት" ማለት የክፍለ ከተማ ወይም የወረዳ ሴቶች፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ነው፡፡
6. "አዋጅ" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 74/2014 ነው፡
7. <u>"ልዩ ድጋፍ"</u>ማለት በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ወይም በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተሰማርተው እገዛ ለሚስፈልጋቸውሴቶች የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ ነው ፡

8. “ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች“ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ስመሆናቸው ከሚመለከታቸው አካል ማረጋገጫ ማቅረብ የሚችሉ ወይም በማህበር ተደራጅተው በማምረትና አገልግሎት በመስጠት ሳይ ተሰማርተው ፈቃድ የተሰጣቸው ወይም ወደ አካባቢያቸው ስመመስስ አቅደው የመጓጓዣ ወጪ እንደሌላቸውበሚቋቋመው ኮሚቴ የተረጋገጠላቸው ወይም ትምህርታቸውን በችግር ምክንያት ስመከታተል ያልቻሉና ልዩ ድጋፍ የሚሹ ሴቶች ነው፡፡

9. “የገንዘብ ድጋፍ“ ማለት ቢሮው ልዩ ድጋፍ ስሚያስፈልጋቸው ሴቶች የሚሰጠውን አስፈላጊውን የገንዘብ ክፍያ ነው፡፡

10. "የቁሳቁስ ድጋፍ" ማለት በዚህ መመሪያ ተጠቃሚ ለሚሆኑ ሴቶች የሚያገለግል የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን ነው፡፡

11. “ቀላል ተስማሚ ቴክኖሎጂ“ ማለት የዕደ ጥበብ ማምረቻና የምግብ ማምረቻ ቀላል ተስማሚቴክኖሎጂ መሳሪያዎች ነው

12. “አደረጃጀቶች ወይም ሲቪክ ማህበራት — ማለት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ተደራጅተው ወይም ተሰማርተው ህጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው የሴት ወይም የወጣት አደረጃጀቶች ወይም የልማት ቡድኖች ወይም እድሮች እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

13. በዚህም መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

### 3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውስጥ ነዋሪ ስሆኑ እና ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች ሳይ ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ዓላማ ፣ልዩ ድጋፍ መስፈርት፣ ድጋፍ አሰጣጥ ፣ ተግባርና ኃላፊነት</u>

### 4. <u>ዓላማ</u>

1. በከተማው ነዋሪ ስሆኑና ልዩ ድጋፍ ስሚያስፈልጋቸው ሴቶች ችግራቸውን አጣርቶ የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ ስማድረግ እና ወጥነት ያስው የአሰራር ስርዓት በመዘርጋት ድጋፍ መስጠት፤
2. በተስያዩ የገቢ ማስገኛ ስራዎች ተሰማርተውየገንዘብ ወይም የመስሪያ ቁሳቁስ ችግር ያስባቸውን ሴቶችን መርዳት፤
3. በእናትና አባት ወይም አንዳቸው ወይም አሳዳጊ ድንገተኛ ሞት ምክንያት ረዳት ሳጡ ሴቶችና ረዳት ስሌላቸው ሴት ተማሪዎች የገንዘብ ድጋፍ ወይም ቁሳቁስ ድጋፍ ማድረግ፤
4. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ የሚገኙ እና በጋራ የመስራት ፍላጎት ሳላቸው ሴቶች የስራና የንግድ ክህሎት ስልጠና እና የመነሻ ካፒታል በመስጠት የሴቶችን የኢኮኖሚ አቅም ስማሳደግ፤
5. በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ስሚገኙ ሴቶች ሰርቶ የእስት ገቢያቸውን ስመጨመር ፍላጎት ሳላቸው ችግረኛ ሴቶች የመስሪያ ቁሳቁስና የስራ ማስጀመሪያ ገንዘብ ድጋፍ በማድረግ የሴቶችን የኢኮኖሚ አቅም መገንባት፡፡

5. <u>ልዩ ድጋፍ ለማግኘት የሚያስፈልግ መስፈርት</u>

የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚነት ለማግኘት የሚከተለውን መስፈርት ማሟላት ይኖርበታል፡-

1. ዕድሜያቸው 18 ዓመት የሞላቸው እና ከዚያ በላይ ለሆኑ ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋት/ቸው ሴት/ሴቶች በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነዋሪ ስለመሆናቸው የወረዳ አስተዳደር መታወቂያ ወይም ከተለያዩ አደረጃጀቶች ወይም ሲቪክ ማህበራት በጽሁፍ የተረጋገጠ ማስረጃ ማቅረብ፤
2. በከተማው ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ሴቶች ለመደገፍ ከሚኖሩበት ወረዳ እና ክፍለ ከተማ አስተዳደር ወይም ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ልዩድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ስለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርቡ፤
3. የልዩ ድጋፍ ፈላጊዎች ሙሉ አድራሻ የቤተሰብ ብዛትና ሁኔታ መገለጽ አለበት፡፡

6. <u>ስለክፍያ እና የቁሳቁስ ድጋፍ አሰጣጥ</u>

1. ልዩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ሴቶች ከወረዳ እስከ ክፍለከተማ ባሉ መዋቅሮች ወይም በሚቋቋመው ኮሚቴ የማጣራት ስራ ከተደረገ በኋላ በቢሮው የበላይ ኃላፊዎች ቀርቦ ሲፀድቅ ብቻ ድጋፉ ይሰጣል፡፡
2. ገንዘብ ወጪ ሆኖ የሚከፈለው በፀደቀው ዓመታዊ የስራ ፕሮግራም መሰረት ለተረጂዎች የሚሰጥ ሲሆን አከፋፈሉም በከተማ አስተዳደሩ የፋይናንስ ህግና አሰራር መሰረት ይሆናል፤
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(2) የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ አስቸኳይ ያልተጠበቀ ሁኔታ ሲያጋጥም ገንዘብ በፋይናንስ አሰራር መሰረት ወጪ ሲደረግ ይችላል፡፡
4. የቁሳቁስ ድጋፍ አሰጣጥ ስርዓት በከተማ ንብረት አስተዳር ህግ አሰራር መሰረት ይሆናል፡፡

7. <u>የበጀት ወይም የሀብት ምንጭ</u>

1. መንግስት ለድጋፍ ከሚመድበው በጀት፤
2. ከአለም አቀፍ ተቋማት ከሚገኝ ድጋፍ፤
3. መንግስት ከሚያገኘው የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ፤
4. ከባለ ድርሻ አካለት ጋር ትስስር በመፍጠር ከሚገኝ ድጋፍ፡፡
5. መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ከሚገኝ ድጋፍ

8. <u>የድጋፍ ኮሚቴው አመሰራረት</u>

የቢሮው ኃላፊዎች ወይም የክፍለ ከተማና የወረዳ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ይህ ተግባር ከሚመለከታቸው ዳይሬክተሮች እና ከክፍያና ሂሳብ ዳይሬክቶሬት ሶስት አባላት ያሉት ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

9. <u>የኮሚቴው ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. ልዩ ድጋፍ የሚያፈልጋቸው ሴቶች ሊያገኙ የሚገባውን የድጋፍ መጠን በሚመለከት የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮ ወይም ለጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ያቀርባል፤
2. ለልዩ ድጋፍየሚቀርበውን ጥያቄ መነሻ በማድረግየአመልካቿን ሁኔታ እና የቀረበውን ማስረጃ ይመረምራል፤ትክክለኛ ድጋፍ የሚገባት መሆኑን ያረጋግጣል፤
3. የተሰጠው ድጋፍ ለታለመት ዓላማ መዋሉን ክትትል ያደርጋል፤
4. ቅሬታበማጣራት የውሳኔ ሀሳብ ለቢሮ ወይም ለጽህፈት ቤት ኃላፊ ያቀርባል፡፡

10. <u>ድጋፍ የሚደረግበት የድግግሞሽ ጊዜ</u>

ችግሩ በተከሰተበት በማናቸውም ጊዜ ሆኖ ድጋፉ በአመት አንድ ጊዜ የሚሰጥ ሲሆን ተጀመረው ድጋፍ በየአመቱ መቀጠል ያለበት መሆኑን ቢሮው ሲያረጋግጥ ድግግሞሹ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

11. <u>ስለ ቢሮው ተግባር እና ኃላፊነት</u>

ቢሮው አግባብነት ባላቸው ህጎች የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. ተገቢውን የክፍያ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ ይፈጽማል፤
2. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኝየድጋፍ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡

12. <u>የክፍለከተማሴቶች፣ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

በሌሎች አግባብነት ያላቸው ህጎች የተሰጠው ስልጣን እና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነትየሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1. ተረጂዎችን በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ይመዘግባል፤
2. የተረጂዎች ልየታ የተደረገባቸውን መዛግብቶች እና የተለያዩ ሰነዶች በጥንቃቄ ይይዛል፣ እንዲያዙ ያደርጋል፤
3. የተረጂዎችን መረጃ በየክፍለ ከተማው ያስተላልፋል፤
4. በቢሮው የሚሰጠውን መመሪያ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡
5. ስለሚደገፉ ተረጂዎች ግልጽ የሆነ ማብራሪያ ይሰጣል፡፡

13. <u>ልዩ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ሴቶች ለመርዳት የሚያስፈልግ የገንዘብ መጠን</u>

1. በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙ ሴቶች ጊዜና ጉልበት ቆጣቢ ተስማሚ ቴክኖሎጅ ግዥ ፈጽሞ ለማሰራጨት የሚያስፈልግ መነሻ የገንዘብ መጠን ለአንድ ሰው 10,000 (አስር ሺህ) ብር የገንዘብ መጠንሆኖ የወቅቱን የገበያ ዋጋ ታሳቢ በማድረግ በቢሮው ማናጅመንት እየተወሰነ የሚሰጥ ይሆናል፤
2. በጋራ ተደራጅተው ለመስራት ፍላጎት ያለቸውና የስራና የንግድ ክህሎት ስልጠና ወስደው አዋጪ በሆነ የስራ መስክ መሰማራት ለሚፈልጉ የመነሻ ካፒታልበቢሮው ማናጅመንት የሚወሰን ሆኖ በ11 ዱም ክፍለ ከተማየሚገኙ የተመረጡ ማህበራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ከመንግስት 10,000 ብር (አስር ሺህ ብር) ከመያድና ከብድርና ቁጠባ ተቋማት በማፈላለግ ሴቶችን በማህበር አደራጅቶ የኢኮኖሚ አቅማቸውን ማሳደግ ይሆናል፤
3. ለትምህርት ክፍያ እና ለትምህርት መርጃ መሳሪያ የሚሆን 2400 (ሁለት ሺህ አራት ብር) መነሻ ሆኖ በቢሮው ማናጅመንት የሚወሰን ይሆናል፤

<u>ክፍል ሶስት</u>

## ስለ ክትትል፣የተከለከሉ ተግባራት እና ቅሬታ አቀራረብ

**14. ስለ ክትትል**

1. ቢሮው፣ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤቶች የድጋፉን የስራ እንቅስቃሴ ይከታተላሉ፣ ይቆጣጠራሉ፣በበላይነት ይመራሉ፤
2. ቢሮው፣ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ሴቶች፣ ህጻናትና ማበራዊ ጉዳይ ጽህፈት ቤቶች ለተጠቃሚ ሴቶች ድጋፉ በትክክል መድረሱን ይከታተላሉ ፣ይቆጣጠራሉ፤
3. የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፍ በአግባቡ ለተረጂዎች ደርሶ ጥቅም ላይ መዋሉን ወርደው ሪፖርት አዘጋጅው ለሚመለከተው አካል ያቀርባሉ፡፡

**15. የተከለከሉ ተግባራት**

1. ማንኛውም ተረጂ ሁለት ጊዜ በመመዝገብ በድጋሚ ድጋፍ መውሰድ የለበትም፤
2. ሀሰተኛ መረጃዎችን በማቅረብ የድጋፍ ተጠቃሚ መሆን ክልክል ነው፤
3. የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፉን ከተፈቀደለት ዓላማ ውጪ መጠቀም የተከለከለ ነው፤
4. የገንዘብ ወይም የቁሳቁስ ድጋፉን ከተፈቀደለት ሴት/ሴቶች ውጪ መጠቀም የተከለከለ ነው፤
5. ማንኛውም ግለሰብ የሚሰጠውን አገልግሎት ማስተጓጎል አይችልም፤
6. በስልጣን፣ በዘር፣በዝምድና፣በትውውቅ ወይም በሀይማኖት መሰረት በማድረግ አድሎአዊ አሰራር መፈጸም የተከለከለ ነው፡፡

**16. የቅሬታ አቀራረብ**

1. ድጋፍ የሚደረግላቸው ሴቶች በአሰራር ሂደት ውስጥ ቅሬታ ሲኖራቸው ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ለወረዳ፣ ለክ/ከተማ እና ለቢሮ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቅሬታቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. ለወረዳው ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት የቀረበው ቅሬታ በሶስት(3) ቀናት ጊዜውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖረበታል፡፡ ለክ/ከተማ ሴቶችና ህጻናት ጉዳይ ጽ/ቤት ለቀረበው ቅሬታ በሶስት(3) ቀናት ጊዜ ውስጥ ምላሽ መሰጠት ይኖርበታል፡፡
3. በክ/ከተማ ሴቶች፣ ህጻናትና ማህበራዊ ጉዳይ ጽ/ቤት ለቅሬታቸው በሚሰጠው ምላሽ ያልረኩ አካላት አቤቱታቸውን ለቢሮ ማቅረብ ይችልሉ፡፡ ቢሮውም ለቀረበው ቅሬታ በአምስት(5) የስራ ቀናት ውስጥ ምላሽ መሰጠት ይኖርበታል፡፡ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**17. ስለተጠያቂነት**

1. የዚህን መመሪያ ድንጋጌዎች የተላለፈ ማንኛውም በየደረጃው የሚገኝ የቢሮው፣ የክፍለ ከተማ እና የወረዳ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ በዲሲፒሊን ተጠያቂ ይሆናል፤
2. ለሁለተኛ ጊዜ መረጃ በማቅረብ ተረጂ ለመሆን በድጋሚ የተመዘገበ ወይም ድጋፍ የወሰደ ማንኛውም ተረጂ በወንጀልና በፍትሀብሄር ተጠያቂ ይሆናል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

18. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው ይህንን መመሪያ ለማስፈጸም የመተባበር ግዴታ አለበት

19. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው መመሪያዎች</u>

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ልማዳዊ አሰራር ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

20. <u>መመሪያውን ስለማሻሻል</u>

ቢሮው እንደ አስፈላጊነቱ ይህን መመሪያ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

3. <u>መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ከተመዘገበበትና በድረ-ገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ዶክተር ሀና የሺንጉስ

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

ሴቶች፣ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ